# የፍየል አይን ከቅጠል የነብር አይን ከፍየል
# የትግል ስልት ስንመርጥ

ሲራክ ከምድረ አሜሪካ ÷ሚድወስት

ቀላል መሆን እኮ የነበረበት ከዲያብሎስ ይልቅ መልዐክን መለየት ነበር። ዛሬ ግን የተቸገርነው ከፉውን ከደጉ ነጥሎ ማውጣቱ ላይ ነው። በተቃዋሚው ጎራ ገና ያልጠራ ስራ አለ። ገዳዩ፣ ሆዳሙ፣ ባንዳው፣ አንጃው፣ ገንጣዩ፣ አጭበርባሪው በሌላ ጎኑ ደግሞ ሃቀኛው ሁሉም ተጨፍልቀው ተቃዋሚ የሚል መልካም ስም ይዘዋል። በርግጥ በፖለቲካ ጎዳና ነጋ ጠባ የሚመላለሱ ማን ሃቀኛ ማን ቀማኛ ፖለቲከኛ እንደሆነ አይስቱትም። የሚያሳዝነው ግን በርካታው ኢትዮጵያዊ ሴረኞችን ለመረዳት ጊዜ ለፈጅበት ይችላል። የዘንድሮዎቹ ቀማኛ ፖለቲከኞች እንኳን ገራገሩን ሕዝብ ቀርቶ ነቃን የምንለውንም የዲያስፖራ ሓበሻዎች እየጋለቡን አይደለምን?

የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሰረታዊ ጠላቱ ወያኔ ነው። ቁጥር አንድ የኢትዮጵያ ጠላት!! ላለፉት በርካታ አመታት ሕዝባችን ግብግቡን ከወያኔ ጋር እንዳይገጥም መሰናክሉን ያበራከቱበት ወያኔዎች ሳይሆኑ ተቃዋሚ በተባለው መልካም ስም ስር የተሰገሰጉት ቀጣፊ ፖለቲከኞች ስለመሆናቸው ጥርጣሬ ውስጥ መግባት የለብንም። ወያኔን መታገል ካቋረጥን ዘመናት አስቆጥረናል እድሜ ለአጭበርባሪ ፓለቲከኞች። መማረሩና መቆጨቱን ትተን ግን ወደ ዋነኛው ጠላታችን ወደ ወያኔ ትግሉን መቃኘት ይጠበቅብናል። ይህ ማለት ደግሞ በዋናነት ወያኔን እየተፋለምን እነሱንም - አወናባጆችንም - በተገቢነቱ ማረቁን መተው የለብንም። በርግጥ ባንድ በኩል ወያኔን ባንድ በኩል አስመሳዩን መታገሉ አንድ ወጥ የሆነውን ኃይላችንን ይከፋፍልብናል። ወያኔን ባጭር ጊዜ ከስልጣን እንዳናነሳው ያደርገናል። የማናመልጠው ሂደት በመሆኑ ትግሉን ጠንከር ጉልበታችንንም ፈርጠም ማድረግ ይኖርብናል።

ላንዳፍታ እንኳን አይናችንን ከወያኔ ላይ ባለማንሳትና የተቀጣጠለውንም ትግል እንዳይበጣጠስ ንቃታችንን ከፍ ወኔያችንን ሞቅ እያደረግን ወደፊት እንጓዝ። እንደ አንዳንድ የዋህ የፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች የፓርላማውን ወንበር ብቻ እያዩ የወያኔን ጥርስ የማያስተውሉ እንደሚኖሩ ሁሉ ብህሎች እንደሚሉት "የፍየል አይን ከቅጠል የነብር አይን ከፍየል" መከሰቱን ደጋግመን ደጋግመን የምናየው ድርጊት ነው። ሲነገራቸውም አያዳምጡም።

በርግጥ ብዙዎቻችን በትግሉ ስልት አመራረጥ ላይ ተለያይተናል። በትግል አመራረጡ ላይ በጣም የተቸገርን ይመስል የቀረቡልን ስልቶች በርክተው እኛንም ሕዝቡንም ግራ አጋብተዋል። በመጀመሪያ ደረጃ የስልጣን ጥያቄ ትግል ይጠይቃል። ትግል ደግሞ የቼዝ ጨዋታ አይደለም ። የስልጣን ጥያቄ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ በመሰሉት አገሮች ውስጥ ትግል ያለደም መካሄ መቻሉ የማታ ሕልም ሳይሆን የቀን ቅዠት ይሆንብኛል። ትግል ስንል ደግሞ የሰላምና የአምጽ ትግል ማለታችን ስለመሆኑ በቅድሚያ ልንስማማ ይገባናል። ትግል የሚጀመረው በተጨቆነው ሕዝብ እንጂ በጠገበውና ስልጣን በያዙት ጥቂቶች አይደለም። ቢሆንለት እኮ ሕዝቡ ከመስራትና በደስታ ከመኖር የበለለጠ አንዳችም ፍላጎት አይኖረውም። ትግል ተገቢና አስፈላጊም ቢሆን ግን መስዋዕትነትን እንደሚያስከፍል አያጠያይቅም። ባልበላ አንጀቱ ላንዲትም ደቂቃ ትግልን ባልመረጠ ነበር መብቱ ተጠብቆለት ቢሆን ኑሮ።

ጭቁኑ ወደ ትግሉ አማራጭ ሲዘጋጅ የቅድሚያ ስልቱ በሰላም መብቱን ለማስከበር ነው። ባገራችን የሰላም ትግል የሰራበት ወቅት አላየሁም። በሰላም መብቱን ለማስከበር የወጣው ሕዝብ በትምክህተኞች ደሙ ሲፈስ ብቻ ነው። ይህ መሆኑ እንደማይቀር ማለትም

ሰላማዊው ትግል የጭቁኑን ደም እንደሚያፈስ እያዩ የምንመርጠው የትግል ስልት ሠላማዊ ነው ለሚሉት ፖለቲከኞችና ድርጅቶች እያዘንኩ ግን የምርጫ መብታቸውን አከብረዋለሁ ባልደግፈውም:: ሕዝባችን ለዘመናት በሰላም መንገድ መብቱን ለማስጠበቅ መሬት ላይ ወድቆ ድንጋይ ተሸክሞ  ለምኗል:: ሰላማዊ ልመናችን ግን አያሌ የሕዝብን ህይወት ቀጥፏል:: ሚርት አይሁንብኝና ይህ አይነቱ ትግል እንኳን ፈጣን ለውጥ ሊያመጣ ቀርቶ ሌላ ዘመናትን ያስቆጥራል ብዬ እፈራለሁ:: እዚህ ላይ ግልጽ ለማድረግ የሚገባኝ ጉዳይ አለ:: የሰላምን መንገድ የያዙ ሁሉ በጥቅሉ እንድ አለመሆናቸውን ነው:: አንዳንዱ በሰላም ስም " የፓርላማ ወንበር ይሰጠኝ" የሚሉና ቀደም ሲል ያቀረብነውን መስፈርቶች ያለው ወያኔ ካልተቀበል ከምርጫው ሳንገባ ግን ትግሉን ወጥረን እንቀጥላለን ያሉትን ደግሞ ከነዚያኞች ጋር ማደባለቅ አይገባም::

በሰላም ልታገል ነው የሚል ድርጅት ስላሙ ሰላም ካሳጣኝስ ምን ማድረግ ይገባኛል ብሎ ማሰብ አለበት:: ለሰላማዊ ትግል በማለት ስንት ህይወት መሰዋት አለበት? የሰላም ትግል ማለት "ቀኝ ፊትህን ሲያጭልህ ግራህን ስጠው አይነት ማለት ይሆን? ቀኜንም ሰጥቼ ጥፊው ባያቆምስ? እንዲያው ለማለት አልኩት እንጅ በሰላሙ ትግል የሚያምኑ እንደዚህ መቀመቅ ወርደው የሚሳሳቱ አይመስለኝም:: ያም ይሁን አይሁን በሰላምም መታገል ጥሩ አጀማመር ሊሆን ይችላል:: ሁሌ ትክክል ነው የሚል እምነት የለኝም:: በሰላም የተጀመረው ትግል ከተጭናገፈና ሆድ የባሰውን ህዝብ ለበለጠ ሶቆቃ ከዳረገው ያ ሰላማዊ ትግሉ ወደማይቀረው ያመጻ ትግል መቀየሩ የትግሉ የተፈጥሮ ዕድገት ደንብ ነው:: ይህ ማለት ደግሞ የሰላምና ያመጻ ትግል ምንኛ የተያያዙ ስለመሆናቸው ካለማመን ከመቾከል ይልቅ አምኖ መቀበሉ የትግሉን ጉዞ ግልጽና ቀና ሊያደርገው ይችላል:: ለዚህም ነው እኮ እነኢሕአፓ የትግሉ ስልት መሆን የሚገባው ሁለ-ገብ ነው የሚሉት::

ስለ ሁለ-ገብ የትግል ስልት <u>ኢሕአፓ</u> እንዲህ ይላል ፥

1. ኢሕአፓ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ በሆኑት የሃገሪቷ ሁኔታና የሕዝቡም መብት ጥቅምና ፍላጎት በሚጠይቃቸው የትግል ስልቶች ይጠቀማል

2. ድርጅቱ ነጻ ሆኖ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል ለማካሄድ ከተቻለ ኢሕአፓ ይህንን ስልት ዋነኛ አድርጎ ይታገላል

3. ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል ለማድረግ በማይቻልበት ሁኔታ ኢሕአፓ ትግል ለማድረግ በማይቻልበት ሁኔታ ኢሕአፓ ትግሉን  በሌሎችም ስልቶች ጭምር ያካሂዳል

4. ኢሕአፓ የሚጠቀምበት ማንኛውም የትግል የሕዝቡን ድጋፍና ሙሉ ተሳትፎ መሰረት ያደረገና በሕዝቡም የታመነበት መሆኑን ያገናዝባል::

ይህን በተመክሮ የዳበረ የትግል ስልት ነበር የዛሬዎቹ አስመሳይ ድርጅት  መሪ ነን ባዮች ኢሕአፓን ጠመንጃ ነካሽ እስከማለት ደርሰው የነበረው:: ዛሬም ገና በውሉ የገባቸው አይመስልም ምክንያቱም የጠመንጃውን ትግል ሲሰብኩ የሰላሙን ትግል አጣጥለውታል:: ካሜሪካን ተራራ ተደብቆ በሪሞት ኮንትሮል ለማዋጋት ብቻ ብር ብር ብር አምጡ ተብለናል፤ ያውም $500:: ብሩን የከፈለም ሰርትፊኬት ይሰጠውልም ተብሎ ይወራ ምናልባት ስልጣን ላይ ከወጡ ያገር መግቢያ ቪዛ መሆኑ ነው መሰል? ለማንኛውም ወገን መሳሪያ ይገቱ ወያኔን እየተፋለምኩ ነው የሚለው ሁሉ የኢትዮጵያ ወዳጅ ነው ወደሚለው ተላላነት እንዳናጋድል መስጋት ተገቢ ነው::

ነጠላ ትግል - የሰላም ትግል ወይም የመሳሪ ትግል ብቻ - ውጤቱ ነጠላ ነው የሚሆነው:: መሆን ያለበት የትግል ስልት ሁለ-ገብ ማለትም በሰላሙም በመሳሪያውም ትግሉ ወያኔን

ማዋከብ ነው ውጤት የሚያስገኘው። ትግሉ የተጣመረ መሆን አለበት። ደም ሳይፈስ ለውጥ ማምጣት አለብን የሚባለው አነጋገር ቅዱስ ቢሆንም እንድ ቀላል ሃቅን ግን ስቷል። አርፎ የተቀመጠው ሕዝብ እኮ እያለቀ ነው ባልፈለገው የተለያየ የወያኔ ጦርነቶች እየተማገደ። ከደርግ ዘመን ጀምሮ እስከ ደረስንበት የወያኔ ዘመን ሕዝባችን እየሞተ ብቻ ሳይሆን አይሞቱ አሟሟት እየሞተ ነው። በተለይ ባሁኑ ወቅት ይህ ሰላማዊ ሕዝብ የሰላም ሰለባ እየሆነ ነው ያለው። ሰላም አረ በስምሽ ስንት ታይቶ የማይታወቅ ግፍ ተሰራብሽ?

ምናልባትም አንደኛውን የትግል ስልት ብቻ ማራመዱ በራሱ በሰላማያዊና በመሳሪያ ትግል መካከል መቀራረብን ሊያርቅ ይችላል የሚል ፍርሃት አለኝ። በነጠላ ክተቀምጡና በትጥቅ ትግል ብቻ ወይም በሰላም ትግል ብቻ የሚል ስልት ከተከተልን ምናልባትም በሁለቱ ስልቶች መካከል ያላስፈላጊ የሆነ ግጭት ወይም ቀውስ ሊከሰትና የትግሉን ትኩረት ከወያኔ ላይ አንስተን በትግል ስልት የታወኩ ድርጅቶችን በመፍጠር ካልተፈለለግ ችግር ውስጥ ያስገባናል። ጸጉር ስንጠቃው ይባባስና ልክ ቀዳሚው ማነው ? እንቁላል ወይስ ዶሮ አይነት ንትርክ ይከተንና ሰላም ወይስ አመጽ የሚሻለው ከሚል ያልተመጣጠነና ጎደሎ ክርክር ውስጥ እንዳንወጣ ሆነን እንጣላለን። ስልቱ መሆን ያለበት ሁለ-ገብ ነው ከተባለ ግን በነጠላው የትግል ስልት አተካሮ ውስጥ አይከተንንም። መስተዋል ያለበት ደግሞ ለምን በሰላማዊ መንገድ ወይም ባመጻ ስልት እንታገላለን ከሚል ድምደማ ሊያደርሰን ከቶም መሞከር የለበትም። የተባለው ከነጠላው ትግል ሁለገቡ ትግል ወሳኝና መሰረታዊ ለውጥን ሊያመጣ የሚያስችል መሳሪያ ነው። በርግጥ በወቅቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለገብ የትግል ስልትን አራምዳለሁ የሚል ኃይል የወያኔን በራኬ ያገኛል የሚል ቅዠት በጭራሽ አይኖረኝም። ትግሌ ሰላማዊ ነው ስለተባለም የወያኔን ቡራኬም ያገኛል ማለትም አይደልም።

አግራችንን ከገባችበት ሲኦል ለማውጣት አማራጩ የትግል ስልት ሁለ-ገብ መሆን ይገባዋል። ትግሉ ሰላማዊ ይሁን ወይስ ያመጽ ከሚል እሰጣገባ ላለመግባት ወገን መንቃት ይገባናል። ካስመሳይ ሰላማውያንና ካወናባጅ ጦረኛ ነን ባዮች መጠንቀቁ ለወያኔ ዕድሜ ማራዘሚያ መንገድ እንዳንከፍት ይረዳናል። የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው የሚል ሰላም ሰባኪ ቦታው ካይማኖት ቤት መሆን እንጂ በፖለቲካው መስክ አይደለም። ብር አምጡ እንጂ ወያኔን ባጭር ቀናት ድባቅ እንመታዋልን ከሚሉም ጦር-አልባ ጦረኞችም ጠንቀቅ ማለት የሚመከር ነው። ጦር-አልባ ጦረኞች ድርጅታቸው ከጅብ የማያስጥል የአህያ ባል አይነት ነው። በልተው ለበላተኛም ይዳርጉናልና ሁሌ ንቁ መሆን ይጠበቅብናል ወገን።

ለነገሩማ በሰላምም አልን ባመጻ ወይም በሁለ-ገብ ለወያኔ ሁሉም አያስደስተውም። ወያኔ ላንዲት ፋታ እንኳን አይኑን ስልጣኔን ይፈታተናሉ ከሚላቸው ድርጅቶች ላይ አልነቀለም። አይነቅልም። ይህን አባባል ለማሳነስ የሚፈልጉ ግለሰችቦችና ድርጅቶች ሊጠነቀቁ ካልቻሉ ብልሆቹ እንደሚሉት “የፍየል አይን ከቅጠል የነብር አይን ከፍየል” የተባልውን አባባል መደጋገምና ማሰማት ይገባል። አባባሉ ግልጽ ካልሆነ - የሞኝ ድርጅቶች አይን ከፓርላማ ወንበር ሲሆን የወያኔ አይን ደግሞ ከሞኞቹ ላይ ነው ለማለት ነው።

ሁለ-ገብ የትግል ስልት ተግባራዊ ይሁን!!!